# አቡነ አፍጼ ገዳም

በገድላቸው መሠረት የትውልድ አገራቸው እስያ ሲሆን አባታቸው አቡድራስ እናታቸው አቅሌስያ ይባላሉ። ወላጆቻቸው ክርስቲያን በመሆናቸው ክርስትና ተነስተዋል። በ15 ዓመታቸው ዲቁና ተቀበሉ። ወዲያውኑ ወደ ግብፅ ሔደው ገዳመ አስቄጥስ ገብተው ሥርዓተ ምንኩስና ተደርሶላቸው መንኩሰዋል። ከዚያም ከ7 ሌሎች መነኮሳት ጋር ሆነው መጻሕፍትንና ንዋየ ቅድሳትን ይዘው ከብዙ ደቀ መዛሙርቶቻቸው ጋር ሆነው ወደ ኢትዮጵያ መጡ።

አክሱም በነበሩበት ጊዜ የኢትዮጵያን ቋንቋን ባሕል አጠኑ። የሚያስፈልገውን ዝግጅት ካደረጉ በኋላ ስብከተ አገራቸውን ተከፋፍለው ተሰማሩ። ለአቡነ አፍጼ የደረሰው የታወቀው ጥንታዊው ከተማ የሓ ነበር። እዚህ ከተማ ጽልሙካ በሚመለከበት የቆየ ምን አልባት በ6ኛው ዓመተ ዓለም ከክርስቶስ ልደት በፊት የታነፀ ቤተ ጣኦት ይገኝበታል። ይህ ሕንፃ አሠራሩ አራት ማዕዘን ሆኖ አቅጣጫው ወደ ምሥራቅ ስለሆነ መግቢያው አንድ በር በምዕራብ በኩል አለው። ምንም እንኳ ሕንፃው ከዕድሜ ብዛት በአንዳንድ ሥፍራ ፈርሶ ቢታይም በጠቅላላው በደህና ሁኔታ ላይ ነው ያለው ለማለት ይቻላል። ስለ ዘመኑ ሕንፃ ሥራ አንድ ዓይነት ሃሳብ ይሰጠናል። ከበሩ በስተቀር መስኮቶች የሉትም። ይህም የጥንት ቤተ ጣኦት ጨለምለም ማለቱን ይመርጣሉ። ምክንያቱም ፍርሃትና አክብሮትን በአማንያኑ ላይ ለማሳደር ሳይሆን አይቀርም።

የዚህ ከተማ ነዋሪዎች አቡነ አፍጼ እስከሄዱበት ጊዜ ድረስ በአምልኮ ጣኦት የተጠመዱ ነበሩ። እሳቸው እዚያ ከደረሱ በኋላ ግን ሁኔታው ተለውጧል። ነዋሪውን አሳምነው አስተምረው አጥምቀዋል። የጣኦት መመለኪያ የነበረውንም ቤተ ጣኦት ወደ ቤተ ክርስቲያን ለውጠው የእመቤታችንን ጽላት አስገብተው ደብረ ሐመልማል ተባለ።[17]

ይህ ሥያሜ እንዴት እንደተሰጠ ገድሉ ሲያብራራ በአካባቢው ውሃ አልነበረምና አቡነ አፍጼ በእጅ መስቀላቸው ባርከው ውሃ አፈለቁ። ሥፍራውም በልምላሜ ተዋጠ ከዚያም በኋላ ደብረ ሐመልማል ተባለ ይላል። አቡነ አፍጼ ያፈለቁት ውሃ ከገዳማቸው አጠገብ ነው። ከእርሳቸው በፊት የተመሠረተ ጥንታዊ ከተማ ያለ ውሃ ኖረ ለማለት አይደለም። የዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ከተሞች ሲመሠረቱ ሦስት አስፈላጊ መስፈርቶች መሟላት ነበረባቸው።

1. በአንድ በኩል ተራራ ወይም ከፍተኛ ቦታ ከተማውን ለመጠበቅ፤
2. በሌላ በኩል የተንጣለለ ሜዳ ለእርሻ ለገበያ የሚያገለግል፤
3. ውሃ ያለበት ሥፍራ ለሕይወታቸው ስለሚያስፈልግ።

እነዚህን መስፈርቶች የሓ አሟልቶ ነው ከተማ የሆነው፤ ተራራ በስተሰሜን በኩል አለው፤ ሜዳም በስተ ምሥራቅ በኩል ተንጣሏል፤ የውሃ ምንጭም አሉት። እዚህ ቦታ አቡነ አፍጼ ገዳም መሥርተው የአንድነት ማኅበር እንዳቋቋሙ ገድላቸው ይናገራል። ይህንን ገዳም ንጉሡ ዐፄ ገብረ መስቀል መጥቶ ጐብኝቶ መተዳደሪያ ርስት ጉልት ሰጥቷል። ከዚህ የሚገኘውን አበል ሲሰው የመነኮሳት ምግብ ይሁን ብለው ንጉሡና ጳጳሱ ስለፈቀዱ ይህም በግዝት ፀንቷል። አቡነ አፍጼ ሕዝቡን እያስተማሩ ሥርዓተ ምንኩስናን እያጠናከሩ ለብዙ ዓመታት ከኖሩ በኋላ በእርጅና እድሜአቸው በዐፄ ገ/መስቀል ዘመነ መንግሥት አርፈው እዚያው የሓ ተቀብረዋል። ከሞታቸው በኋላም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ አድርጋቸዋለች፤ ለክብረ በዓላቸው ተስማሚ የሆነ ቀለም ቅዱስ ያሬድ ሠርቶላቸዋል፤ እስመለዓለም አንገርጋሪ፣ ዚቅ ደርሶላቸዋል፤ የእኚህ ጻድቅ ገድል በብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት የሚገኝ የኢትዮጵያ ቅርስ ነው።[18]